ሥነ ፍጥረት ክፍል ፩ ለሰንበት ት/ቤት ሕፃናት የተዘጋጀ።

ሥነ ፍጥረት ክፍል ፪ ለትላልቅ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች የተዘጋጀ።

የዚህ መጽሐፍ ሽያጭ ገቢው ከኅትመት ዋጋ የተረፈውን ለስብከተ ወንጌል ሥልጠና መረሐግብር እና ለበጎ አድራጎት ሥራ የሚውል ነው።

ዋጋው 5.50

# ሥነ ፍጥረት

## ክፍል ፫

ለከፍተኛ የመንፈሳዊ ትምህርት ተማሪዎች የተዘጋጀ

ከዲያቆን ክፍያለው ታደሰ
ኅዳር ፲/፫ ፲፱፻፺ ዓም

www.ethiopianorthodox.org

ሪታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

# ሥነ ፍጥረት

## ክፍል ፩

ለከፍተኛ የመንፈሳዊ ትምህርት ተማሪዎች የተዘጋጀ

ከዲያቆን ከፍያለው ታደሰ
ኅዳር ፲/፲ ፲፱፻፺፲ ዓም

www.ethiopianorthodox.org

መካር ረዳት ይሻል። ሥላሴ ግን ይህን ሁሉ አይሹም የሰው ባሕርይ ይራባል፣ ይጠማል፣ የሥላሴ ባሕርይ ግን የማይጠማ፣ የማይራብ፣ የማይደክም ነው። ሰው ልሰወር ባለ ጊዜ አጽር ቅጽር ይሻል ሥላሴ ግን ይህን ሁሉ አይሹም የገዛ ባሕርያቸው ይሰውራቸዋል። ሰው ልገለጽ ባለ ጊዜ ፋና ብርሃን ይሻል ሥላሴ ግን ይህን ሁሉ አይሹም በገዛ ባሕርያቸው ይገለጻሉ ሰው በሕይወቱ ሞት በመንግሥቱ ሕልፈት አለበት ሥላሴ ግን በሕይወታቸው ሞት በመንግሥታቸው ሕልፈት የለባቸውም። የቀረውን ፍጥረት ለምን ፈጠሩት ቢሉ ለእኛ ልንበላው ልንጠጣው ልንማርበት ልንሠራበት ነው። ላሙን፣ በጉን፣ ፍየሉን፣ አዝርዕቱን፣ አትክልቱን ፣ ማሩን፣ ወተቱን እንበላዋለን እንጠጣዋለን ፈረሱን በቅሎውን እንጠቀምባቸዋለን ዕፅዋቱን ባሕር እንዳንጠልቅ በገደል እንዳንወድቅ እንሻገርበታለን። የፀሐይ፣ የእሳት፣ የውሃ ሦስትነት አላቸው እኛም በነዚህ ምሳሌነት የሥላሴን አንድነት ሦስትነት እናውቅባቸዋለን ከፍጥረቱ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማይፈጽም የለም። እግዚአብሔርን ማወቅ ከፈለግህ መምህርና ምስክር ሆኖ ወደሚያስረዳህ ሥነ ፍጥረት ተመልከት ጠቢቡ በጥበቡ ደራሲ በድርሰቱ ባለሞያ በተግባሩ እንደሚታወቅ ሁሉ እግዚአብሔርም ለፍጥረቱ በፍጥረቱ ይታወቃል ራሱን ያለ ምስክር አልተወም እንዳለ ሉቃስ የሐዋ.ሥራ 14:17 «ወዘኢይትአወቅ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትአወቅ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ በአእምሮ ወለብዎ» እንዳለ ኤጲፋንዮስ ሥላሴ ግን ከምሥጋና በቀር





የሚፈልጉት የለም እስከዚህ መቅደም ነው። ከዚህ ቀጥሎ የየዕለቱን ፍጥረታት በዝርዝር እንመለከታለን ።

## ዕለተ እሑድ

1ኛ. በመጀመሪያ ሰዓት እግዚአብሔር አራቱን ባሕርያት ለምን ፈጠረ? ቢሉ ለባህርዩ አራት ነገራት እንዳሉ እወቅ ሲል ነው ኃያል ነኝ ሲል እሳትን ፈጠረ እሳት ውሃ ካልከለከለው ሁሉን ያጠፋል ጌታም ቸርነቱ ካልከለከለው ላጥፋ ቢል ይቻለዋል። እስመ አልቦ ነገር ዘይሠዓኖ ለእግዚአብሔር እንዳለ ገብርኤል። ሉቃ. 1፡37 ፈታሒ ነኝ ሲል ነፋስን ፈጠረ ነፋስ እህልን ከገለባ ይለያል። ጌታም ምዕመናንን ከመናፍቃን ጻድቃንን ከኃጥአን ይለያል። መንጽሔ ነኝ ሲል ውሃን ፈጠረ ውሃ እድፍን ከአካል አካልን ከእድፍ ይለያል ጌታም ነፍስን ከኃጢአት ኃጢያትን ከነፍስ ይለያል። «ወሐበነ ማየ መንጽሔ ዚአነ» እንዳለ በኪዳን ባዕል ነኝ ሲል መሬትን ፈጠረ ከመሬት ብዕል ሥጋዊ ይገኛል። ምድር ከሃሊ ናት ፍጥረቱን ሁሉ ችላ ትኖራለች ጌታም ከሃሊ ነው የፍጥረቱን ሁሉ ኃጢአት ክፋት ችሎ ታግሶ ይኖራል። «ኃያል ወመሥተዓግሥ» መዝ. 7፡11 /ኃይለኛም ታጋሽም ነው/ እንዳለ ክቡር ዳዊት በባሕርዩ ያሉ አራቱን ነገራት ለመጠየቅ አራቱን ባሕርያት ፈጠረ። እነዚህንም አንድ ጊዜ በመላ አልፈጠራቸውም በፊት ጥቂት እሳት ጥቂት ነፋስ ጥቂት ውሃ ጥቂት መሬት ፈጠረ። እሊህም በፈቃደ እግዚአብሔር ተሚልተው ይሸናነፋሉ። እሳት ውሃን



www.ethiopianorthodox.org

ያፈላዋል ውሃ ነፋስን ይገታዋል ይገድበዋል ነፋስም መሬትን ይበትነዋል። ለማስታረቅ ግን ሦስት ሦስት ግብር ያላቸው አድርጓቸዋል። የእሳት መደቡ ብርሃን ሲሆን ውዕየት ይብስት አለው የውሃ መደቡ ብርሃን ሲሆን ቁረት እርጥበት አለው ቁረት ውዕየት አለው የመሬት መደቡ ጽልመት ሲሆን ይብስት ርጥበት አለው ሲያስታርቃቸውም እሳትን በብሩህነት ከነፋስ በርጥብነት ከመሬት ነፋስን በይቡስነት ከመሬት ውሃን በብሩህነት ከእሳት በቁርነት ከነፋስ በርጥብነቱን ከመሬት ነፋስን በጽሉምነቱ ከመሬት በውዕይነቱ ከእሳት በርጥብነቱ ከውሃ አዋሕዶ አስማምቷቸዋል።

ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያስተምረን ብርሃን ከመፈጠሩ በፊት በመጀመሪያ ጨለማ ነበር በዚህም የጨለማ ሰዓት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ፍጥረታት ተፈጥረዋል፤ ስለዚህም ጨለማ እንደ አንድ ሥነ ፍጥረት የመጀመሪያ ፍጥረት ተቆጥሯል፡ በኦሪት ዘፍጥረት ም.1፡2 ጨለማ በጥልቁ ላይ ነበር ይላል።

እግዚአብሔር ሰባቱን ሰማያት ፈጠረ።

በ2ኛ. ሰዓተ ሌሊት ከእሳት ወዕየቷን ትቶ ብርሃኗን ነስቶ ከአጽናፍ ጉዝጉዞ ዘረጋ ይህ ኪሩቤል የተሸከሙት ዙፋን ነው። ሰማይ ውዱድ ይባላል።

በ3ኛ. ሰዓተ ሌሊት ሰማይ ውዱድን እንደ መሠረት አድርጎ በላይ መንበረ ስብሐትን ፈጠረ ሥራዋ እንደቤተ መቅደስ አራት ማዕዘን ነው ከጽንፍ እስከ ጽንፍ አትደርስም





በመጠን ናት ሰው የያዘውን ዓለም ታህላለች በዚህም ሥላሴ ለጻድቃን ለሰማዕታት በዘፈቀደ ይታዩበታል ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋርዶ ሰባት የእሳት ቅጽር ቀጽሮላታል።

በ4ኛ. ሰዓት ከእሳት ብርሃኗን ነስቶ ከብርሃን ብርሃንን ጨምቆ አጽሮት በመንበረ ስብሐት ላይ ጽርሐ አርያምን እንደባጥ እንደጣፈር ሠርቶ በፍጥረቱ ሁሉ አምሳል የብርሃን ሳጋ የብርሃን ቀለም ሸለማት ከሰማይ ሁሉ በላይ ናት ከርሷ በላይ ሌላ የለም ዳርዋን መጨረሻዋን ከሥላሴ በቀር የሚያውቅ የለም። ይኸውም የሰማይ ውዱድ ቅጽር ከጽርሐ አርያም ቅጽር እርሱ ባወቀው ማኅተም አትሞ ገጥሞታል።

በ5ኛ. ሰዓት ከእሳት ብርሃኗን ነስቶ ከአድማስ እስከ አድማስ ዘርግቶ ኢዮር የሚባል ሰማይ ፈጥሮ ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋርዶ ሰባት የእሳት ቅጽር ቀጽሮ የኢዮርን ቅጽር እርሱ ባወቀው ማኅተም አትሞ ገጥሞታል።

በ6ኛ ሰዓት ከእሳት ብርሃኗን ነስቶ ከአድማስ እስከ አድማስ ዘርግቶ ራማ የሚባለውን ሰማይ ፈጥሮ ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋርዶ ሰባት የእሳት ቅጽር ቀጽሮ የራማን ቅጽር ከኢዮር ቅጽር እሱ ባወቀው ማኅተም አትሞ ገጥሞታል።

በ7ኛ ሰዓት ከእሳት ብርሃኗን ነስቶ ከአድማስ እስከ አድማስ ዘርግቶ ኢዮር የሚባል ሰማይ ፈጥሮ ሰባት የእሳት መጋረጃ



www.ethiopianorthodox.org





የተሸለመ፣ ስድስት ክንፍ ያላቸው፣ መብረቅ ነጐድጓድ ለብሰው የሚኖሩ፣ ብሩህ ደመና ተጐናጽፈው የሚኖሩ፣ እግራቸው አምደ እሳት የመሰለ እና በእግራቸው በክንፋቸው ባሕር የሚያግዱ መላእክት አሉ መጠናቸውን ግን ከሥላሴ በቀር የሚያውቀው የለም ::

12 ሰዓተ ሌሊት 12 ሰዓተ መዓልት 24ቱ ጊዜአት እለተ እሁድ ደረሰ ይህች እሁድ በሥላሴ ዘንድ አንዲት ዕለት ናት በእኛ ዘንድ ሺ ዘመን ናት። እሁድ ማለት አንድ ማለት ነው። አንድ ዕለት 8 ፍጥረት ድረስ እሊህ 12 ሰዓተ ሌሊት 12 ሰዓተ መዓልት እግዚአብሔር ሥራውን የሠራባቸው ናቸው እንጂ በከንቱ የመጡ አይደሉም እስከዚህ ድረስ የእሁድን ሥነ ፍጥረት ይናገሯል።

## ዕለተ ሰኑይ

እግዚአብሔር በዕለተ ሰኑይ በቀዳሚት ሰዓተ ሌሊት ጠፈር ይሁን ውሃም ከውሃ ይለይ ብሎ ቢያዘው ከዚህ እስከ ብሩህ ሰማይ ሞልቶ የነበረውን ውሃ ከአራት ከፍሎ አንድን እጅ በመካከል ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ዘርግቶ እንደ ቤተመንግሥት አዳራሽ ወደላይ ጠበብ አድርጎ እንደብረት አጽንቶ ፈጠረው ይኸ የምናየው ሰማይ ነው ጠፈር ይባላል ጠፈር ማለት ሥዕል ማይ ማለት ነው።



www.ethiopianorthodox.org

-ብ ጢስ ተጠቅልሎ ወጽቶ አንድ ደመና ሆኗል፣ ይህን ደመና ጠቅልሎ ለናጌብ አለበሳት እሳትና ነፋስ ግቡኡ ውስተ መካናቲከሙ እንዳለ ከዚህ በታች ያሉትን ዓላማት ሲያዘጋጁ ጥቂት ነፋስ ከፍቶታል። እሳቱ ለመፍቀደ ሰብእ ነፋሱ ውሃውን ለመቅደስ አዝርዕቱን ለመቀስቀስ ለሥጋ ለነፋስ የሚፈጠረውን ለማናፈስ እሳትን ፈጥሮ ነፋስን ሲተው ከላህቡ ብዛት ከዋዕዩ ጽናት የተነሳ ፍጥረቱ ሁሉ በተቃጠለ ነበር ነፋስን ፈጥሮ እሳትን ቢተው ከቁሩ ብዛት ከውርጩ ጽናት የተነሳ ፍጥረቱ ሁሉ ባረረ በተኮማተረ ነበርና የነፋሱን ቁረት በእሳቱ እያሞቀ የእሳቱን ውዕየት በነፋስ እያበረደ ፍጥረቱን ሁሉ አስማምቶ ይኖራል እሳትና ነፋስ ቀሊላን ናቸው ነፋስና እሳት ደግፈው ባይዟቸው ኖሮ ወርደው ከበርባሮስ በተጨመሩ ነበር፣ እሊህም ሲመላለሱ ፍጥረቱ ሁሉ ባለቀ ነበርና ስለዚህ ጌታ በጥበቡ አደጋግፎ አሠፈራቸው «ወኩሉ በጥበበ ገብርከ» እንዳለ ክቡር ዳዊት ብርሃን ከእሳት እንደተገኘ ጨለማ ከበርባሮስ ተገኝቷል። ይኸን ጨለማ ሌሊት ይሆን ዘንድ ሠርክ ሲሆን ከምዕራብ ባሉት መስኮቶች ወጽተህ ይህችን ዓለም ሸፍነሐት አድረህ ጎህ ሲሆን ወደ እናትህ ወደ በርባሮስ ግባ ብሎ አዘዘው ብርሃን ጎህ ሲሆን ጨለማን በምዕራብ ባሉት መስኮቶች ገብቶ ይውላል፣ «ወመልአ ብርሃን ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም» እንዳለ ዕዝራ ጨለማ ሠርክ በምዕራብ ባሉት መስኮቶች ወጽቶ ብርሃን ገፍቶ በምሥራቅ ባሉ መስኮቶች እስከ ጠፈር ድረስ ሞልቶበት ያድራል። ብርሃንና ጨለማ በፈቃደ እግዚአብሔር እየተሸናነፉ





ይኖራሉ እንጂ ሁለቱ በአንድ ጊዜ አይገኙም «መኑዘደመሮ ለብርሃን ምስለ ጽልመት ወለጽድቅኒ ምስለ ኃጢአት» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ 2ኛ ቆሮ. 6:14 ሰኑይ ማለት ሁለተኛ ዕለት ማለት ነው ሁለት ዕለት ዘጠኝ ፍጥረት ደረሰ።

## ዕለተ ሠሉስ

እግዚአብሔር በዕለተ ሠሉስ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት «ለታብቅል ምድረ ሐመልማል ሣዕር ዘይዘራዕ በበዘርዑ ወበበዘመዱ» ብሎ ቢያዝ አዝርዕት አትክልት ዕጽዋት 3 ፍጥረት ተፈጠሩ ብሩህ ብሩህን መሬት በምሥራቅ ከናጌብ ወዲህ ጠቅልሎ አኑሮ ገነት ትተከል ብሎ ቢያዝ ያች መሬት ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ ብላ ገነት ተተከለች። በገነት መካከል ዕጸ ሕይወትን ተከለ ጫፏ እስከ ሰማይ ይደርሳል ፍሬዋ እንደ ሮማን ፍሬ ከእግር እስከ ራሷ ሙሉ ነው። ጣእሟ መዓዛዋ ያለ ደዌ ያለሕመም ነፍስ ከሥጋ ትለያለች። ከፍሬ አንዲቱን ፍሬ ጉርሶ አላምጦ ሳይውጡ እንደቀድሞው ፍሬ ተክቶ ይገኛል። ጣዕሙ ከአፍ መዓዛው ካፍንጫ ሳይለይ ሰባት ቀን ይኖራል። ፍሬዋን የቀመሱ ሰዎች እንደዚህ ያለ ምግብ ከእግዚአብሔር ቸርነት በቀር ለፍጡር ባልተገባም እያሉ ያደንቃሉ፣ ከዕጸ ሕይወት ሥር ማየ ሕይወትን አወጻ ከወተት ሰባት እጅ ትነጻለች ከመዓር ከስኳር ሰባት እጅ ትጣፍጣለች፣ ከአራቱ ዓበይት ዕፅዋት ሥር አራቱን አፍላጋት ስማቸው ግዮን፣ ኤፌሶን፣ ጠግሮስ፣ ኤፍራጥስ ይባላሉ፣ በአራቱ ማዕዘን



www.ethiopianorthodox.org

ተመሳቅለው ገነትን ያጠጣሉ የምሥራቅ ውሃ ወደ ምዕራብ ያጠጣል፣ በምዕራብ ያለው ውሃ ወደ ምሥራቅ ያጠጣል፣ በሰሜን ያለው ውሃ ወደ ደቡብ በደቡብ ያለው ወደ ሰሜን ያጠጣል እሊህም በገነት ሳሉ ግዮን ወተት፣ ኤፌሶን ወይን፡ ጤግሮስ ማር፣ ኤፍራጥስ ዘይት ናቸው:: ግዮን የኢትዮጵያ፣ ኤፌሶን የአንጾኪያ፣ ጤግሮስ የቆስጥንጥንያ፡ ኤፍራጥስ የሮም ውሃ ነው:: በገነት በምዕራብ ለአዳምና ለኛም ሞት ያፈራችልን ዕፀ በለስን ተከለ::

ገነትን ታላላቁን ታናናሹን ቅጠል አብቅይ ብሎ አዘዛት በገነት ያሉ አዝርዕት አትክልት ዕፅዋት ታላላቁ ቅጠላቸው 70 እና 80 ክንድ ይሆናል ምን ቢያንስ ከአሥራ ሁለት ክንድ አያንስም ፍሬያቸው ታላላቅ ጋን መክደኛ ያህላል እንደ ብር እንደ ቀለበት ክብ ነው ይኸውም እንደ ከዋክብት ያበራል ጣዕሙ ከአፍ መዓዛው ከአፍንጫ ሳይለይ ሰባት ቀን ይቀመጣል:: በገነት ያሉ አዝርዕት አትክልት ዕፅዋት ማን ይመገባቸዋል ቢሉ ብሔረ ብፁአን ያሉ ጻድቃን አዕዋፍ ይመገቧቸዋል፣ ማን ያመላልሳቸዋል ቢሉ ገነትን ለማናፈስ ለምዕራብ የተሾመ ነፋስ አለ በዘጠነኛው ሰዓተ መዓልት አሻቅቦ ወደ ምሥራቅ በነፈስ ጊዜ እንደ ዝናም ያዘንምላቸዋል ያን እየተመገቡ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ይኖራሉ፣ አዝርዕት አትክልት ዕፅዋት በራሳቸው የሚያፈሩ አሉ:: በጫፋቸው የሚያፈሩ አሉ በሥራቸው የሚያፈሩ በልጃቸው በሚስታቸው





የሚጠቀሙ፣ በጉድናቸው የሚያፈሩ በገረዶቻቸው በሎሌያቸው የሚጠቀሙ፣ በጫፋቸው የሚያፈሩ ጥረው ግረው ራሳቸውን የሚጠቅሙ አምሳል ናቸው:: ይህ ስሙ ነው ወርቁ ግን በሥራቸው የሚያፈሩ በጌታ ትምህርት ያመኑ በጉድናቸው የሚያፈሩ በሐዋርያት ስብከት ያመኑ በጫፋቸው የሚያፈሩ በሌሎች መምህራን ትምህርት ያመኑ የምዕመናን አምሳል ናቸው:: አንድም በሥራቸው የሚያፈሩ በጌታ ልደት አምነው ክርስቶስን በኩር ያሉ በጉድናቸው የሚያፈሩ ውሃ ተጠምቀው በመስቀሉ የፀኑ በጫፋቸው የሚያፈሩ ሞቱን ትንሣኤውን አምነው በመስቀሉ የጸኑ አምሳል ናቸው፣ አንድም በሥራቸው የሚያፈሩ የባለ 100 ክብር አምሳል ናቸው:: አንድም በጉድናቸው አፍርተው ፍሬአቸውን ከአዕዋፍ ሰውረው የሚኖሩ አሉ በራሳቸው አፍርተው ፍሬአቸውን አዕዋፍ በልተዋቸው የሚቀሩ በጉድናቸው አፍርተው ፍሬአቸውን ከአዕዋፍ ሰውረው የሚኖሩ ብዙ ትሩፋትን ምግባራት ሠርተው አብልተው አልበሰው አላበላንም አላለበስንም እያሉ ያደረጉትን ሰውረው በወዲያ ዓለም የሚጠቀሙ ናቸው:: በራሳቸው አፍርተው ፍሬአቸውን አዕዋፍ በልተዋቸው የሚቀሩ ብዙ ምግባር ትሩፋት ሰርተው በከንቱ ውዳሴ ተጎድተው በወዲያ ዓለም የማይጠቀሙ አምሳል ናቸው፣ ካንድ መሬት ወይንና ሙዝ ሬትና መርዝ ይበቅላሉና እንዲሁም ከአንዱ አዳም ኃጥአንና ጻድቃን ተገኝተዋል:: ወይንና ሙዝ የጻድቃን፣ እሬትና መርዝ የኃጥአን አምሣል ናቸው::



www.ethiopianorthodox.org

የሆነውን አይተው ይህችንስ ዕፁብ ድንቅ ፍጥረት ለፍጡር አልሰጣትም የአጼ ፈንታ እንዲሉ የርሱ ፈንታ ናት ብለው ሙሽራውን ፈጣሪዋን አመሠገኑ፣ የሥላሴ ፍጥረት ስንኳን መላዕክት እግዚአብሔር ስንኳን የፈጠረው ዓለማቱን አይቶ ደስ አለው «ወርዕየ እግዚአብሔር ከመሰናይ» እንዳለች ኦሪት ፀሐይና ጨረቃን በስንት ማዕረግ በስንት ኬክሮስ ፈጠራቸው? ቢሉ ፀሐይን ሦስት ማዕረግ ሦስት ኬክሮስ ከፍ አድርጎ በምዕራብ በኩል በጊዜ ሠርክ ፈጠረ ጨረቃን አምስት ማዕረግ አምስት ኬክሮስ ዝቅ አድርጎ በምሥራቅ ፈጠረ ፀሐይ አብርታ ስትገባ ጨረቃ ስትወጣ ተያይተዋል።

ፀሐይ በምዕራብ ገብታ በሰሜን ዙራ በምሥራቅ ወጥታ መዓልቱን ገዝታ ስታበራ ዋለች። ጨረቃ ሌሊቱን ገዝታ ስታበራ አደረች ከዋክብት ግን የጨረቃ ተከታይ ናቸው፣ ፀሐይ መዓልትና ሌሊቱን ብታበራ ከዋዕዩ ፅናት የተነሣ ፍጥረት ሁሉ በተቃጠለ ነበርና፣ ጨረቃ ሌሊቱን መዓልቱን ብታበራ ከቁሩ ብዛት ከውርጭ ጽናት የተነሣ ፍጥረት ሁሉ በተኮማተረ ነበርና ስለዚህ ለፀሐይ መዓልቱን ለጨረቃ ሌሊቱን አሰለጠናቸው፣ ፀሐይ የጻድቃን አምሣል ናት በብርሃኗ ፀንታ እንድትኖር ጻድቃንም በደግ ምግባር ፀንተው ይኖራሉና፣ ጨረቃ የኃጥአን ምሣሌ ናት በሙሉ ብርሃን ተፈጥራ ስትጎድል ስትሞላ እንድትኖር ተነሣህያንም አንድ ጊዜ ወደ ኃጢአት አንድ ጊዜ ወደ ጽድቅ ሲሄዱ ይኖራሉ፣ አንድም ፀሐይ ጨረቃ





የመምህራን ምሣሌ ናቸው ሰሌዳውን ከእሳት ከውሃ እንደ መድረግ መምህራንም ተናደው ታግሰውም ያስተምራሉና ጨረቃ ጠፍ ባደረገች ቀን ራሷን ወስዳ ከፀሐይ እግር ትቀብራለች፣ መጋቢ ብርሃን መልአክ ከወደላይ ብርሃን እያመጣ ይስልባታል፣ ጨረቃ ራሷን ከፀሐይ እግር እንድትቀብር በቃሁ ነቃሁ ብሎ ሚመተ ክህነት ገንዘብ ማድረግ አይገባምና መጋቢ ብርሃን መልአክ ከወደላይ ብርሃን እያመጣ እንዲስልባት መሾም ከበላይ ካለ ነውና ከሊቀ ጳጳስ ነውና፣ ከዋክብት የምዕመናን አምሳል ናቸው። ከአንገታቸው በላይ በሰው አምሳል አቆልቁለው ሰውን እንዲያዩ አድርጓቸዋል በብርሃን እንዲበላለጡ ምዕመናንም በክብር ይበላለጣሉና «ኮከብ እመኮከብ ይሄይስ ክብሩ» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ 1ኛ ቆሮ. 15:35 ከአንገታቸው በላይ በሰው አምሳል ማድረጉ መሾም ከሰው ወገን ነውና አቆልቁለው ሰውን እንዲያዩ ማድረግ መሾም ሕዝቡን ለማገልገል ነው። እስመ ካህናቱ አዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር እንዳለ ፀሐይ መዓልቱን ጨረቃ ሌሊቱን ከዓመት እስከ ዓመት አብርተው ገዙ።

ከዋክብትስ ማን አስገዛቸው ቢሉ መገብተ ዕለት ሰባት ናቸው። ሸምሽ፣ ቀመር፣ አጠርድ፣ መሪህ፣ መሻተሪ ዘኅራ ዙሐል ይባላሉ። እሊህ ከእሁድ እስከ ቅዳሜ ይመገባሉ። መገብተ አውራህ አሥራ ሁለት ናቸው። አልሐመል፣ አልሰውር፣ አልጀሙዛ፣ አልሸርጣን፣ አልአሳድ፣ አልሰንቡላህ፣



www.ethiopianorthodox.org

አልሚዛን፣ አልአቀረቡ፣ አልቀውስ፣ አልዚደፍ፣ አልደለው፣ አልሁት ይባላሉ:: እሊህ ከመስከረም እስከ ነሐሴ አንድ አንድ ወር ይመግባሉ::

አራት ሊቃነ ከዋክብት አሉ፣ ዓመቱን ከአራት ተከፍለው 365 ቀን ይመገባሉ እሊህም ከርክኤል ናርኤል መልኤል እለመልማክ ይባላሉ፣ ከመጋቢት 26 ቀን እስከ ሰኔ 25 ከጳጉሜን 1 ቀን ጨምሮ 91 ይሆናሉ ይህንን መልኤል ይገዛል ፀደይ ይባላል ለፀደይ ሰልጥኖ የነበረ ቁር ፈጽሞ ሲጠፋ ወደታች ተቀብሮ የነበረ ዋዕይ ወደላይ ሲል ምድር ትሞቃለች የዘሩባትን ታበቅላለች ከሰኔ 26 ቀን እስከ መስከረም 25 ቀን ጳጉሜን 1 ቀን ጨምሮ 91 ይሆናል ይህንን ሕልመልማልክ ይገዛል ክረምት ይባላል:: በክረምት ሰልጥኖ የነበረ ዋዕይ ፈጽሞ ሲጠፋ ተቀብሮ የነበረ ቁር ፈጽሞ ሲወጣ ተቀብሮ የነበረው ከውሃው ብዛት የተነሣ ምድር እፈርስ እፈርስ ትላለች ጌታም ፀሐይን አውጥቶ ያፀናታል ከመስከረም 26 ቀን እስከ ታኅሣሥ 25 ቀን ከጳጉሜን 1 ቀን ጨምሮ 91 ይሆናል:: ይህንን ከርስኤል ይገዛል መፀው ይባላል፣ በመጸው ሰልጥኖ የነበረ ቁር ፈጽሞ ሲጠፋ ተቀብሮ የነበረ ዋዕይ ፈጽሞ ሲወጣ ከዋዕዩ ብዛት የተነሣ አዝርዕት አትክልት ይደርቃሉ፣ ታጭደው ተወቅተው ይገባሉ:: ከታኅሣሥ 26 ቀን እስከ መጋቢት 25 ቀን ጳጉሜን አንድ ቀን ጨምሮ ዘጠና አንድ ቀን ይሆናል:: ይህን ናርኤል ይገዛል ሐጋይ ይባላል:: ይህቺ ከጳጉሜን የቀረች አንዲቱ ቀን





ዕለተ መግባ ትባላለች በዓመት የልደት ዕለት ትውላላች ጌታ የተወለደባት ቀን ናት፣ ዛሬ ሰው ሠርግ ሲያሰናዳ በፊት መብሉን መጠጡን ምንጣፉን አሰናድቶ ኋላ ሰውየውን እንዲጠራ ጌታም ይህን ዓለም ሲፈጥረው በአድማስ ደግፎ ደመና ከፍክፎ ዝናማቱን በደመና ጭኖ ነፋሳትን አሸክሞ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብትን መባርቅትን ነጎድጓድን ለመላእክት አሳያቸው መላዕክትም አቤቱ እንዲህ አድርገህ ፈጥረህ ለምንህ ነው? ቢሉት ያች ያያችኋት እየሩሣሌም ሰማያዊት እንግዲህ ለምፈጥረው ለአዳም ሥፍራው ቦታው ናት፣ እነዚህ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት የሚያበሩለት ፋናዎች መብራቶች ናቸው፣ እነዚህም ነፋሳት ደመናት ውሃ የሚቀዱለት ባሮች ናቸው፣ እነዚህም መባርቅት ነጎድጓድ የሚበላውን የሚጠጣውን አዝርዕቱን አትክልቱን እንዲያብቡ እንዲያፈሩ የሚያደርጉለት ናቸው፣ ይህችም ምድራዊ ገነት ግንቡ መናገሻው ናት አላቸው፣ መላእክትም አቤቱ አዳም ያልከው አካሉ ማንን ያህላል? መልኩ ማንን ይመስላል? ብለው ቢጠይቁት አካሉ ከእናንተ እጅግ ያንሳል መልኩ ግን እኔን ይመስላል በእኔ አምሳል እፈጥራለሁ ሲላቸው እጅግ ደስ አለቸው አቤቱ ፈጥረህ አሳየንና እርሱን መልኩን አይተን ያንተን መልክ እንድናየው እንድናውቀው አሉት፣ ዲያብሎስ ይህንን ቢሰማ የማያልቅ ፍርሀት ቅንአት አደረበት ደግሞም እንዲህ አለ በአዳም ምክንያት ብዙ መከራ ያገኛል ብዬ እፈራለሁ ስለዚህ ቀድሞ እፈጥራለሁ ብዬ ያስብኳትን እሳት ልፈትናት ቢሆን



www.ethiopianorthodox.org

ማለት ከሕቱም ምድር በነፍስ ሕያው ሆኖ የተገኘ ልጅ ማለት ነው። አንድም ሕያው እግዚአብሔር እምህበ አልቦ አምጥቶ የፈጠረው ልጅ ማለት ነው። እሊህም እሳት ነፋስ በአዳም የሚኖሩ ደመ ነፍስ ናቸው እስመ ነፍስ ታኀድር በደም እንዳለ ደመነፍስ እንደሆነ ሲያጠይቅ «ኢትብልኡ ደመ እስመ ነፍስ ታኀድር በደም ደመ ነፍስ ሥጋክሙ ይእቲ» ይላል ብርንዶ /ጥሬ/ ሥጋ አትብሉ። ነፍሳቸውን ጨምራችሁ ትበላላችሁ ሲል ብርንዶ ሥጋ አትብሉ አለ። እነሆ ሰው በሕይወቱ ደህንነቱ መታወቁ በመሞቁ በመተንፈሱ ነው ሙቀቱ እሳትንፋሱ ሲለየው ግን ሕይወት ደህንነት የለውም የመሬት ግብሩ ግዙፍ ነው ሥጋ ቁርበቱ ግዙፍ አካል የሚሆነው መሬት ነው የውሃ ግብሩ ርጥበት ነው ደም ምራቅ አንብዕ ሆኖ የሚፈስ ውሃ ነው። አራዊትስ ግዙፋን ናቸው ደመ ነፍስ ይኖራቸዋል የዕፅዋትስ አላቸው ማለት ነው? ቢሉ እንደየግብሩ የማይዋለድ የለም።

አዝርዕት አትክልት ዕፅዋት በተተከሉ ጊዜ በሥራቸው 20 እና 30 ይወልዳሉ በጫፋቸው አንድ እልፍ እና ሁለት እልፍ ያፈራሉ በነፋስነታቸው ይናወጻሉ በእሳትነታቸው ሲሰብቋቸው እሳት ይወጣቸዋል በውሃነታቸው ሲቆርጧቸው ውሃ ደም ይወጣቸዋል በመሬትነታቸው ተቆርጠው በወደቁ ጊዜ አፈር ትቢያ ይሆናሉ እሊህም አራቱ ባሕርያት ብቻ አልፈጠሩትም። እንደ ሥጋ የማትታመም የማትሞት ሦስት ነገራት

ሪታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት



ያላት ነፍስ ጨምረው ፈጥረውታል እሊህም ለባዊነት፣ ነባቢነት፣ ሕያውነት ናቸው።

በአዳም በአካለ ሥጋው በአካለ ነፍሱ መቀዳደም አለበት፣ ቢሉ የለበትም መቀዳደምስ ቢኖርበት ንግበር ሥጋ ወንግበር ነፍስ ባሉ ነበር ሥላሴ ዓለሙን ሁሉ ሲፈጥሩ በእግራቸው ሄደው በእጃቸው ይዘው አልፈጠሩም ይሁን ያሉት ሁሉ ይሆንላቸዋል አዳምን ይፈጠር ብለው ቢያዙ አራቱ ባሕሪያተ ሥጋ /ሥጋነቱ/ ሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ አንድነት ተዋሕደው የ30 ዘመን ጎልማሣ ሆኖ አንድ ጊዜ ተገኝቷል። ስብእ ማለት 4ቱ ባሕርያተ ሥጋ ሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ናቸው አዳም ማለት ነቀፋ የሌለበት ሥግው እመሬት ፍጹም መልከ መልካም ማለት ነው። ሥላሴም አዳምን ፈጥረው ድካም፣ ንዋም፣ ንቃህ፣ ትጋህ የሚስማማው አድርገውታል ድካም፣ ንዋም የሥጋ፣ ንቃህ፣ ትጋህ የነፍስ ግብር ነው አዳምም እንስሳት አራዊት ሁለት ሁለት እየሆኑ ሲወጡ ሲወርዱ አይቶ ሥላሴ ከመላእክት በቀር ሴትና ወንድ እያደረጉ ፈጥረዋል ምነው እኔን ብቻዬን ፈጠሩኝ ብሎ አሰበ ሥላሴም እጓለ እምሕያው ብቻውን መኖር አይገባውም ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘይረድኦ እንዳለ ዘይረድኦ ማለቱ ግን ገና በወንድ አካል ያለች ናትና መርዳትስ እንዴት ነው ቢሉ ልጅ በማስገኘት፣ ከፍትወት፣ ከብቸኝነት ትረዳዋለችና አዳምም እጅግ ቢነቃ በተሰማው ነበር። እጅግም ቢተኛ ይህች ሴት ከየት መጣች?



www.ethiopianorthodox.org

## ታሪከ አዳም

መላእክትም የብርሃን መጐናጸፊያ የብርሃን ጫማ የብርሃን አክሊል ዘውድ ሸልመው በሠረገላ ብርሃን ላይ አኑረው በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ሆነው በአምሣለ ንጉሥ አክብረው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘገብሮ ለአዳም እያሉ ወስደው በገነት አኖሩት ሔዋንንም መላእክት እየጠበቋት 80 ቀን ተቀመጠች በተፈጠረች በ80 ቀን እንደ አዳም ከሥላሴ ልጅነት ተወለደች የፀጋ መንግሥትን ነገሰች መላእክት የብርሃን መጐናጸፊያ የብርሃን ጫማ የብርሃን አክሊል ዘውድ ሸልመው በገነት ከአዳም ጋር አኖሯት ዛሬ ወንድ በ40 ቀን ሴት በ80 ቀን ክርስትና መነሳታቸው በአዳምና በሔዋን አንጻር ነው ያን ጊዜ አዳምና ሔዋን የተቀበሉትን መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ሴትና ወንድ በክርስትና ይቀበሉታል። አዳምና ሔዋን በዚህ ፀጋና ክብር በገነት ሰባት ዓመት ኖሩ ።

ስለምን ሥላሴ እንስሳና አራዊትን አጒንብሰው በአራት እግራቸው እንዲሄዱ አድርገው ፈጥረው አዳምን አቅንተው ፈጠሩት ቢሉ ጌታ ሎሌውን እመቤት ገረዷን ነገራቸውን በትህትና እንዲሰሟቸው እንስሳ አራዊትም የአዳም ተገዥዎች ምድራዊያን ናችሁ ተስፋ ትንሣኤ የላችሁም ሲል ነው አዳምን ግን ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ መካከለኛ ገዥ ነህ ሰማያዊ ነህ ተስፋ ትንሣኤ አለህ ሲሉ እንደ ዘንግ መልምለው እንደ እሸት ፈልፍለው አሸቅቦ እንዲሄድ አደረጉት። እንስሳ አራዊት በሠርክ ሲፈጠሩ ሰንብተው ስለምን አዳምን በነግህ ፈጠሩት ቢሉ ሠርክን ጨለማ ይከተለዋል እናንተም ጽሉማነ አእምሮ ናችሁና ጽልመት ሞት ይከተላችኋል በምድር ፈርሳችሁ በስብሳችሁ ትቀራላችሁ ሲል እንስሳትንና አራዊትን በሰርክ ፈጠረ። ዳግመኛም ለይኩን ብርሃን፣ ለይኩን ጠፈር፣ ለታብቁል ምድር፣ ለይኩን ብርሃናት፣ ለታውጽእ ባሕር፣ ለታውጽእ የብስ፣ እያሉ ሲፈጥሩ ሰንብተው ስለምን አዳምን ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሣሊነ ብለው ፈጠሩት ቢሉ ይህስ ለዲያብሎስ ዘለፋ ነው። ሹመቱ ማዕረጉ ከሁሉ በላይ ነበርና የክብሩን ብልጫነት አይቶ ይህን ሁሉ ዓለም የፈጠርሁ እኔ ነኝ አለ ሥላሴም ተቆጥተው ገሃነም እሳት ቢያወርዱት እግዚአብሔር እንደኔ ያለ ዕፁብ ድንቅ ፍጥረት አያገኝምና ታርቆ ሀገሬ ይመልሰኛል ብሎ ይመኝ ነበር። ሥላሴ ግን እኛ በባሕርይ የገዛነውን በጸጋ የሚገዛ እንደኛ በነፍሱ ሦስትነት ያለው ሕያው ሆኖ የሚኖር ክቡር ፍጥረት እንፈጥራለን ሲሉ «ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሣሊነ» ብለው ፈጠሩት ሥላሴም አዳምና ሔዋንን በገነት ያሉ አዝርዕት አትክልት ዕፅዋትን ብሉ ጠጡ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያሉ ፍጥረት ሁሉ ይገዛላችሁ። ነገር ግን ክፉና መልካም የምታሳይ አንዲት ዕፀበለስ አለች እሷን አትብሉ እሷን የበላችሁ እንደሆነ የሞት ሞት ትሞታላችሁ ከእኔ ትለያላችሁ ገሃነም እሳት ትወርዳላችሁ አላቸው እንስሳትንም ጌታችሁ አዳም በገነት ተሾሞላችኋል ሂዱ





www.ethiopianorthodox.org

